የገንዘብ ሚኒስቴር

**MINISTRY OF FINANCE**

# መመሪያ ቁጥር 1151/2019

# በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሂሳብ ስረዛ አፈፃፀም መመሪያ

# Directive 1151/2026

# Federal Government Owned Enterprises Writeoff Implementation Directive

**መስከረም፣ 2019 ዓ.ም**

**September,2026**



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

**<u>መመሪያ ቁጥር 1151/2019</u>**
**<u>በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሂሳብ ስረዛ አፈፃፀም መመሪያ</u>**

የሆልዲንግ ኩባንያው እና ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቶች ከተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባር አንዱ በባለቤትነት ለያዟቸው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ዘመናዊ የኩባንያ አስተዳደር ሥርዓት እንዲዘረጉ ማድረግና አላማቸውን ለመወጣት የሚያስችላቸውን የአሰራር ሥርዓቶችን መዘርጋት በመሆኑ፤

በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሂሳብ ሪፖርቶቻቸው ላይ ለረዥም ጊዜ ሲንከባለሉ የቆዩ እንዲሁም በበቂ ሁኔታ የተረጋገጡ የማይሰበሰቡ ሂሳቦች፣ የማይከፈሉ ሂሳቦች እና ዋጋ የሌላቸው ወይም የሚወገዱ ንብረት ሂሳቦች ግልፅነትንና ተጠያቂነትን በሚያሰፍን መልኩ ለመሰረዝ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓትን መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት ለሂሳብ ስረዛ ሂደት ግልጽ የሆኑ መርሆችን፣ ሁኔታዎችን፣ ኃላፊነቶችን፣ ዘዴዎችን እና የአጸዳደቅ መዋቅሮችን መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የገንዘብ ሚኒስቴር በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1314/2016 አንቀጽ 13(21) እና አንቀጽ 47(2) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

**<u>Directive 1151/2026</u>**
**<u>Federal Government Owned Enterprises Writeoff Implementation Directive</u>**

WHEREAS, one of the powers and duties entrusted to the Holding Company and the Supervising Authority is to ensure the establishment of a modern corporate governance system and to issue policies and working procedures that enable the State-Owned Enterprises (SOEs) under their ownership to achieve their objectives;

WHEREAS, it has become necessary to lay down a clear operating system that allows for the write-off of uncollectible receivable accounts, unpaid account payable balances, and assets with no realizable value or disposable assets , which have been accumulating in the financial reports for a long time and are sufficiently substantiated, in a manner that promotes transparency and accountability;

WHEREAS, it is essential to define transparent principles, conditions, responsibilities, methods, and approval structures for the write-off process in accordance with International Financial Reporting Standards;

NOW, THEREFORE, the Ministry of Finance has issued this Directive pursuant to the power vested in it under Article 13(21) and Article 47(2) of the Federal Government Owned Enterprise Proclamation No. 1314/2024.

Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "በፌዴራል መንግስት ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሂሳብ ስረዛ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 1151/2019" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ ወይም የኃረጉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"አዋጅ"** ማለት በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት የተያዙ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1314/2016 ነው።
2) **"ድርጅት" ወይም "ድርጅቱ"** ማለት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የልማት ድርጅት ነው።
3) **"ዋና ሥራ አስፈጻሚ"** ወይም **"ዋና ሥራ አስኪያጅ"** ማለት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ የመንግሥት የልማት ድርጅት በበላይነት ለመምራት ኃላፊነት የተሰጠው ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ፕሬዚዳንት ወይም ተመሳሳይ የኃላፊነት ደረጃ ያለው ሰው ነው።
4) **"ተሰብሳቢ ሂሳቦች"** ማለት ለድርጅቱ ዕዳ ያለባቸው ማናቸውም መጠኖች ሆነው ገንዘብን ወይም ሌላ ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን የመቀበል ከሕግ ወይም ከውል የሚመነጭ መብትን የሚጨምር ሲሆን፣ ይህም ለዕቃዎች ወይም ለአገልግሎቶች የሚከፈሉ የንግድ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን፣ የተሰጡ ብድሮችን፣ የሠራተኛ ቅድመ ክፍያዎችን፣ የሥራ ማስኬጃ ቀሪ ሂሳቦችን፣ የፕሮጀክት ቅድመ

## Chapter One
## General Provisions

1. **Short Title**

This Directive may be cited as the **"Federal Government Owned Enterprises Write-off Implementation Directive No. 1151/2026."**

2. **Definition**

Unless the context otherwise requires, the following definitions shall apply for the purpose of this Directive:

1) **"Proclamation"** means the Federal Government Owned Enterprise Proclamation No. 1314/2024.
2) **"Enterprise"** or **"the Enterprise"** means a state-owned enterprise.
3) **"Chief Executive Officer"** or **"General Manager"** means the person responsible for the overall leadership of the State-Owned Enterprise, having the status of Chief Executive Officer, President, or similar level of authority.
4) **"Receivables"** means any amounts owed to the Enterprise as a legal or contractual right to receive money or other economic benefit, including trade receivables for goods or services, loans provided, staff advances, imprest balances, project advances, deposits, penalties, interest, and any other monetary claim recorded as an asset.



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

ክፍያዎችን፣ ተቀማጭ ሂሳቦችን፣ ቅጣቶችን፣ ወለዶችን እና በማናቸውም ሌላ መልክ እንደ ሀብት ተመዝግበው የሚገኙ የገንዘብ ጥያቄዎችን ያጠቃልላል።

5) **"ተከፋይ ሂሳቦች"** ማለት ድርጅቱ ለተረከባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች፣ ለተበደረው ገንዘብ፣ ለውል ጥያቄዎች ወይም በሂሳብ መዝገብ ላይ ለተመዘገቡ ሌሎች ግዴታዎች ለአቅራቢዎች፣ ለአገልግሎት ሰጪዎች፣ ለአበዳሪዎች፣ ለሥራ ተቋራጮች፣ ለብድር ሰጪዎች፣ ለሠራተኞች፣ ለመንግሥት አካላት ወይም ለማንኛውም ሦስተኛ ወገን ገንዘብ የመክፈል ወይም ግዴታዎችን የመወጣት ኃላፊነቶች ነው።

6) **"የሂሳብ ስረዛ"** ማለት አንድ ሀብት ወይም እዳ ተጨማሪ የኢኮኖሚ ጥቅም የማይገኝበት ወይም የመክፈል ግዴታ የሌለበት መሆኑ በዚህ መመሪያ በተደነገገው አሰራር ሥርዓት መሰረት በጥናት እና በሰነድ በተደገፈ ማስረጃ ሲረጋገጥ፣ እንዲሁም ማናቸውም ምክንያታዊ የሆኑ የገቢ አሰባሰብ፣ የማስገደጃ እና የሂሳብ ማስታረቂያ እርምጃዎች ተሟጥጠው ሲጠናቀቁ ከሂሳብ መዛግብት ውስጥ በቋሚነት እንዲወገድ ማድረግ ነው።

7) **"ንብረት"** ማለት የረዥም ጊዜ ንብረትን እና ክምችትን ጨምሮ መንግሥት የልማት ድርጅቱ የተያዙ ንብረቶች እና ሀብቶች ናቸው።

8) **"ክምችት"** ማለት በመደበኛ የንግድ ሥራ ውስጥ ለሽያጭ የተያዘ ንብረት፤ ወይም ለእንደዚህ ዓይነቱ ሽያጭ በማምረት ሂደት ውስጥ የሚገኝ ንብረት፤ ወይም በምርት ሂደት ወይም በአገልግሎት አሰጣጥ

5) **"Payables"** means obligations of the Enterprise to pay money or settle obligations to suppliers, service providers, creditors, contractors, lenders, employees, government bodies or any third party for goods or services received, funds borrowed, contractual claims, or other liabilities recorded in the books.

6) **"Account Write-off"** means the permanent removal of an asset or liability from the accounting records when it is confirmed, through investigation and documented evidence based on the procedures established under this Directive, that no further economic benefit or settlement obligation exists, and all reasonable recovery, enforcement, and reconciliation measures have been exhausted.

7) **"Assets"** means property or resources controlled by the Enterprises including inventory or stock and non-current assets.

8) **"Inventory"** includes assets held for sale in the ordinary course of business; or assets in the process of production or modification for such sale; or materials or supplies to be consumed in the production process or in the rendering of services and raw materials or components acquired for operational use.



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ዕቃዎች ወይም አቅርቦቶችን ያጠቃልላል።

9) **"የረጅም ጊዜ ንብረት"** ማለት በድርጅቱ ቁጥጥር ሥር ያለ፣ በዋናነት ለቀጣይ የሥራ እንቅስቃሴ አገልግሎት ወይም ለረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንት የተያዘ የድርጅቱ የኢኮኖሚ ሀብት ሲሆን፣ ንብረቱን ለማስወገድ ውሳኔ ከመወሰኑ አስቀድሞ በድርጅቱ መደበኛ የሥራ ዑደት ውስጥ ወደ ገንዘብ ይቀየራል፣ ይሸጣል፣ ወይም ጥቅም ላይ ይውላል ተብሎ የማይጠበቅ ነው። ይህም ማሽኖች፣ ተሽከርካሪዎች፣ መሣሪያዎች፣ የቤት ዕቃዎች፣ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሣሪያዎች፣ የተያዘ ንብረት፣ ከፕሮጀክት ጋር የተያያዙ በሂደት ላይ ያሉ ሥራዎች፣ እንደ ሶፍትዌር ፈቃዶች እና ፓተንቶች ያሉ የማይዳሰሱ ንብረቶች፣ እንዲሁም ሌሎች ቋሚ ንብረቶችን ያካትታል።

10) **"መጠባበቂያ"** ማለት የአንድ ሀብት እድሜ፣ ጥራት፣ ሁኔታ እና ሊሰበሰብ የሚችልበት እድል ተተንትኖ ከሚጠበቀው ወይም ሊደርስ ከሚችል ኪሳራ፣ ከጥራት መበላሸት ወይም ካለመሰብሰብ አኳያ የሂሳብ ስረዛ ከመጽደቁ በፊት በሀብቱ የተመዘገበ ዋጋ ላይ የሚደረግ ቅነሳ ማለት ነው።

11) **"አጣሪ ኮሚቴ"** ማለት ለስረዛ የቀረበን ማንኛውንም ሀብት ወይም እዳ ለመመርመር፣ ማስረጃዎችን ለማረጋገጥ፣ መንስኤዎችን እና ተጠያቂ ወገኖችን ለመለየት፣ ግኝቶችን ለማዘጋጀት እና የውሳኔ ሃሳቦችን ለቦርዱ ለማቅረብ

9) **"Non-current Assets"** is a long-term economic resource controlled by the enterprise that is acquired or held primarily for continuing operational use or long-term investment, and is not expected to be realized, sold, or consumed, within the Enterprise's normal operating cycle prior to the decision to dispose of the asset. It includes machinery, vehicles, equipment, furniture, ICT equipment, acquired asset, project-related work-in-progress, intangible assets such as software licenses and patents, and other long-term.

10) "**Provision"** means the reduction in the recorded value of an asset to reflect expected or probable loss, deterioration, or unrecoverability determined through analysis of age, quality, condition, and collectability, prior to approval of write-off."

11) "**Investigation Committee"** means a temporary committee established under this Directive for the purpose of examining any asset or liability proposed for write-off, verifying evidence, assessing causes and responsible parties, preparing findings, and submitting recommendations to the Board."

12) Words and phrases to which meanings are assigned in the Proclamation shall also be applicable to this Directive.



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

በዚህ መመሪያ መሠረት የሚቋቋም ጊዜያዊ ኮሚቴ ማለት ነው፡፡

12) በአዋጁ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሐረጎች ለዚህም መመሪያ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

13) በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

1) ይህ መመሪያ በመንግሥት ባለቤትነት በተያዘ ማንኛውም የመንግሥት የልማት ድርጅት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከባንክ ሥራ ጋር በተገናኘ ብቻ ይህን መመሪያ አግባብነት ካለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ጋር በተጣጣመ መልኩ ማስፈፀም አለባቸው፡፡

3) በዚህ መመሪያ መሠረት የሚደረግ የሂሳብ ስረዛ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ወይም ሌላ አግባብነት ያለው ተቋም ግዴታው እንዲቀር በግልጽ የሚፈቅድ ውሳኔ ካልሰጠ በስተቀር ኃላፊነት ላለባቸው ወገኖች እንደ ዕዳ ምህረት ተደርጎ አይቆጠርም።

13) In this Directive, any term expressed in the masculine gender shall also include the feminine gender.

## 3. Scope of Application

1) This Directive shall be applicable to any Federal Government Owned Enterprise.
2) Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, the Commercial Bank of Ethiopia and the Development Bank of Ethiopia shall implement this directive in a manner consistent with the relevant directive of the National Bank of Ethiopia concerning only banking business.
3) Write-off under this Directive shall not constitute debt forgiveness for responsible parties unless a competent court or authorized institution issues a decision expressly authorizing such release.



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

## ክፍል ሁለት
## ተሰብሳቢ ሂሳብን ከሂሳብ መዝገብ ስለመሰረዝ

### 4. ተሰብሳቢ ሂሳቦች ስለሚሰረዙበት ምክንያቶች

ተሰብሳቢ ሂሳብ ከሚከተሉት በአንዱ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ምክንያቶች ከመዝገብ ሊሰረዝ ይችላል፦

1) ዕዳ ያለበት ድርጅት በኪሣራ ምክንያት ሲዘጋና የተዘጋው ድርጅት የሂሳብ አጣሪዎች ድርጅቱ የነበሩበትን እዳዎች ከሀብቱ መክፈል እንዳልተቻለ በፍርድ ቤት ማረጋገጥ ሲቻል፣ ወይም
2) ባለዕዳው ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይና በንብረት አጣሪው በሕግ የሚከበር ንብረት አለመኖሩ ማረጋገጥ ሲቻል፣ ወይም
3) ባለዕዳው ሲጠፋ ወይም ከአገር በመጥፋቱና አግባብነት ባለው አጣሪ በሕግ የሚከበር ንብረት አለመኖሩ ማረጋገጥ ሲቻል፣ ወይም
4) ከባለዕዳ ጋር በተከሰተ አለመግባባት ፍርድ ቤት የተሰብሳቢ ሂሳቡ መከፈል እንደሌለበት ሲወስን፤ ወይም
5) ከባለዕዳ ጋር በተከሰተ አለመግባባት ወይም በሌላ ምክንያት ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ወይም ስልጣን ላለው የዳኝነት አካል መውሰድ ከገንዘብ አንፃር አዋጭ አለመሆኑን የመንግሥት የልማት ድርጅቱ ዳይሬክተሮች ቦርድ ሲያምንበት እና ተሰብሳቢው አስር ዓመትና ከዚያ በላይ የቆየ ሲሆን፤

## Chapter Two
## Write-Off of Receivables from the Book of Accounts

### 4. Grounds for Write-Off of Receivables

Receivables may be written-off based on one of the following reasons፡

1) When the indebted organization is closed due to bankruptcy and the liquidators of the closed organization can confirm in court that the organization's liabilities could not be settled from its assets; or
2) When the debtor passes away and it can be confirmed by the liquidators that there is no legally recognized property; or
3) When the debtor disappears or absconds from the country, and it can be confirmed by the relevant liquidators that there is no legally recognized property; or
4) When the court rules that the receivable should not be paid due to a dispute with the debtor; or
5) Where the Board of Director of the Enterprise believes that taking the matter to court or a competent judicial body due to a dispute with a debtor is not viable in terms of time and cost and the receivable has remained outstanding for ten years or more; or
6) When an investigation confirms that the receivable arose from fraud, error, or missing



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

6) ምርመራ ተካሂዶ ተሰብሳቢ ሂሳቡ በማጭበርበር፣ በስህተት ወይም በሰነድ መጥፋት ምክንያት የተፈጠረ መሆኑ ሲረጋገጥ እና ኃላፊነት ያለበት ወገን በሕግ ወይም በአካል ሊታወቅ ወይም ተጠያቂ ሊደረግ የማይችል ሲሆን።

7) ሌሎች ተመሳሳይ ከአቅም በላይ የሆኑ እና በሆልዲንግ ኩባንያው ወይም በተቆጣጣሪው ቦርድ የታመነባቸው ምክንያቶች።

## 5. <u>ተሰብሳቢ ሂሳቦች የሚሰረዙበት አፈፃፀም</u>

የመንግሥት የልማት ድርጅት ማንኛውንም ተሰብባቢ ሂሳብ ከመዝገብ ሲሰርዝ የአጣሪ ኮሚቴ በማቋቋም እና የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸውን በማረጋገጥ መሆን አለበት፡-

1) ከባለዕዳው ለመንግሥት የልማት ድርጅት ተመላሽ ሊሆን የሚገባ ሂሳብ ለማስመለስ በመንግሥት የልማት ድርጅቶቹ ዳይሬክተሮች ቦርድና ማኔጅመንት በኩል የተደረገ ጥረት መኖሩንና ለመሰብሰብ አስቸጋሪ ሆኖ መገኘቱን እንዲሁም የመንግሥት የልማት ድርጅቱ አስፈላጊ የማስመለስ እርምጃ መወሰዱን ማስረጃ ማቅረብ ሲቻል፤

2) የመንግሥት የልማት ድርጅቱ ከባለዕዳው ጋር የገባውን የውል ሰነድ እና ተያያዥነት ያላቸውን ሰነዶች ማቅረብ፤ ወይም የውል ሰነድ እና ተያያዥነት ያላቸውን ሰነዶች ከመንግሥት የልማት ድርጅት ቁጥጥር ውጪ ማቅረብ

documentation and the responsible party cannot be legally or physically identified or held liable.

7) Other similar force majeure events and reasons accepted by the Board of the Holding Company or the Supervising Authority.

## 5. <u>Implementation of Write-Off of Receivables</u>

When a State-Owned Enterprise writes off any receivable account from its books, it shall do so by establishing an investigating committee and ensuring that the following conditions are met:

1) The existence of evidence proving that effort was made by the Board of Directors and Management of the State-Owned Enterprises to recover the amount due from the debtor, that the matter was deemed to be uncollectible and that the State-Owned Enterprises took necessary action፡
2) Presentation of the amount of the debt to be written off and the contractual document between the State-Owned Enterprises and the debtor, and associated documents; or, if the contractual document and associated documents cannot be provided due to reasons beyond the control of the State-Owned Enterprises, explaining this in writing to the Board of Directors;
3) Confirmation of the existence of a Receivable Aging Analysis prepared based on the aging period of the State-Owned



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

ሳይቻል ሲቀር ይህንኑ በጽሁፍ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ማስረዳት፤

3) በመንግሥት የልማት ድርጅት የተሰብሳቢ ሂሳቦች የቆይታ ጊዜ ላይ ተመስርቶ የተሰራ የዕድሜ/ የቆይታ ጊዜ ትንተና መኖሩን ማረጋገጥ እና የግምገማውን ውጤት ከሂሳብ ላይ እንዲሰረዝ ከተጠየቀው ጠቅላላ መጠን ጋር መመርመር፣

4) የተሰብሳቢ ሂሳቦችን እድሜ እና ስጋት ግምገማ መሠረት በማድረግ ከስረዛ በፊት የመጠባበቂያ ሂሳብ መመደብ፤

5) ከባለዕዳው የሚፈለግ ሂሳብ ከመዝገብ ተሰርዞ ወደፊት ክትትል ሊደረግበት በሚያስችል መልኩ የሚያዝ መሆኑን፤

6) የሂሳብ አጣሪ ኮሚቴው መደበኛ ምርመራ ማካሄዱን እና ለቦርዱ ሪፖርት ማቅረቡን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፤ እና

7) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1-5) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የልማት ድርጅት ተሰብሳቢ ሂሳቡ የማይሰበሰብ መሆኑ ሲረጋገጥ የሂሳብ ስረዛውን በሚከተለው አግባብ ማከናወን አለበት፡-

ሀ) ተሰብሳቢ ሂሳብን ከመዝገብ በሚሰረዝበት ወቅት በመንግሥት የልማት ድርጅቶች የተሰብሳቢ ሂሳቦች የቆይታ ጊዜ ላይ የተመሠረተ የእድሜ ትንተና መዘጋጀት አለበት፤

ለ) ሂሳቡ በትክክለኛው ግዴታ ወይም ውል መሠረት መሰብሰብ በነበረበት የጊዜ ገደብ ላይ በመመስረት አጠራጣሪ ሂሳቦችን መለየት እና አስቀድሞ

Enterprises's receivables, and examination of the assessment result against the total amount requested for write-off;

4) Establishment of a provision prior to write-off based on the aging and risk assessment of receivables;

5) Ensuring that the account sought from the debtor, once written off the books, is maintained in a manner that allows for future follow-up.

6) Confirmation that the Account Investigation Committee has conducted a formal investigation and submitted a report to the Board.

7) When it is confirmed that receivables are uncollectible, the write-off process shall be executed by the Enterprise according to the following strategy:

(a) At the time of writing off the receivables from the books, an aging analysis must be prepared based on the aging period of the State-Owned Enterprises' receivables.

(b) Based on the deadline by which the receivables should have been collected according to the proper obligation or agreement, doubtful receivables should be identified, and a provision (reserve account) should be set aside first.

(c) Only after the provision is recognized shall the receivables be submitted for write-off approval.

(d) Accounting adjustments shall be recorded at the time of approval using proper accounting



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

የተጠራጣሪ ሂሳቦች መጠባበቂያ መያዝ አለበት፤

ሐ) ተሰብሳቢ ሂሳብ ለስረዛ ውሳኔ ሊቀርብ የሚችለው መጠባበቂያ ከተያዘለት በኋላ ብቻ ይሆናል፤

መ) የሂሳብ ማስተካከያዎች ስረዛው በሚጸድቅበት ወቅት ተገቢ የሆኑ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ዘዴዎችን በመጠቀም መመዝገብ እና በሚቀጥሉት የፋይናንስ መግለጫዎች ላይ መገለጽ አለባቸው።

## 6. ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ከመዝገብ የመሰረዝ ሥልጣን

ለስረዛ የሚቀርቡ ተሰብሳቢ ሂሳቦች በተሰብሳቢው ሂሳብ መዝገብ ባለው የገንዘብ መጠን ላይ ተመስርቶ በሚከተለው አግባብ ይሰረዛል፡-

1) የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ፡-

ሀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 እና 5 የተደነገገውን ሳይከተል የገንዘብ መጠናቸው እስከ ብር 10,000 /አስር ሺ/ የሆኑ ሊሰበሰቡ የማይችሉ መሆናቸውን ያመነባቸው ጥቃቅን ተሰብሳቢ ሂሳቦችን በተናጠል ከመዝገቡ የመሰረዝ ስልጣን አለው፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) የተጠቀሰው ቢኖርም በአንድ የፋይናንስ ዓመት የጠቅላላ የጥቃቅን የተሰብሳቢ ሂሳብ ድምር መጠን ከብር 500,000 /አምስት መቶ ሺ ብር/ ሊበልጥ አይችልም።

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) መሰረት የተሰረዙ ሂሳቦች ዝርዝር በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለልማት ድርጅቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት መደረግ አለባቸው።

entries, and reflected in the subsequent financial statements.

## 6. Power for Write-Off of Receivables

Receivable accountss presented for write-off shall be written-off based on the monetary amount recorded in the accounts receivable ledger in the following manner:

1) The Chief Executive Officer (CEO) of the Enterprise:
   a) has the authority to individually write off petty uncollectible accounts receivable up to the amount of Birr 10,000 (Ten Thousand), without following the provisions set forth in Articles 4 and 5 of this Directive, where the CEO is satisfied that they are uncollectible.
   b) Notwithstanding the provisions of sub-article 1(a) of this Article, the total aggregate amount of petty receivable accounts written off in a single financial year may not exceed Birr 500,000 (Five Hundred Thousand).
   c) Receivables written off pursuant to sub-article 1 (a) of this Article must



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

2) የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ በስሩ ለሚገኙ የልማት ድርጅቶች በሚሰጠው የደረጃ ምደባ መሰረት ደረጃ 1 የሆነ የልማት ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃሚ፡-

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሰረት ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ሊሰርዝ ይችላል፤

ለ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 እና 5 የተደነገገውን በመከተል በአንድ ፋይናንስ ዓመት የገንዘብ መጠናቸው እስከ ብር 50,000,000 /ሃምሳ ሚሊዮን/ የሆኑ ሊሰበሰቡ የማይችሉ መሆናቸውን ያመነባቸው ተሰብሳቢ ሂሳቦችን የመሰረዝ ስልጣን አለው፤

3) የመንግሥት የልማት ድርጅት የዳይሬክተሮች ቦርድ መሰብሰብ የማይችሉ ሂሣቦችን ከመዝገብ እንዲሰረዙ የመወሰን ስልጣን አለው፤ አፈፃፀሙም እንደሚከተለው ይሆናል፡ -

ሀ) የሚሰረዘው ሂሳብ በአንድ ፋይናንስ አመት ውስጥ ጠቅላላ መጠን ድርጅቱ በፋይናንስ ዓመቱ የመጀመሪያ ቀን ላይ ካለው ከተከፈለ ካፒታል እስከ 1% /አንድ መቶኛ/ ወይም ከብር 100,000,000 /አንድ መቶ ሚሊዮን ብር/ ከሁለቱ አነስተኛ የሆነው የብር መጠን ድረስ።

ለ) ቦርዱ በአጣሪ ኮሚቴው ተጣርቶና በቦርዱ የኦዲት ኮሚቴ የውሳኔ ሃሳብ ተደግፎ የቀረበለትን የተሰብሳቢ ሂሳብ ስረዛ ጥያቄ ከገመገመ በኋላ ቢያንስ በሰላሳ ቀናት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት።

ሐ) ቦርዱ የሂሳብ ይሰረዝልኝ ጥያቄውን በከፊልም ይሁን ሙሉ በሙሉ ያጸደቀው እንደሆነ፤ ለመሰረዝ ያበቃውን የግዴታ ምክንያት፣ የጸደቀበትን ቀን፣ ከሂሳቡ የተሰረዘውን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ ጽሑፍና ሌሎች አስፈላጊ እና አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች በማያያዝ

be reported to the Board of Directors of the Enterprise within a period of one month.

2) Chief Executive Officer of Tier 1 enterprise, as categorized by the Ethiopian Investment Holdings for the enterprises under its management:

a) May write off accounts receivable in accordance with the provisions of sub-article 1 of this article;

b) Has the authority to write off accounts receivable which they have determined to be uncollectible, up to a monetary value of ETB 50,000,000 (fifty million) per fiscal year, by following the provisions set forth in Articles 4 and 5 of this Directive.

3) The Board of a State-Owned Enterprise shall have the authority to decide on the write-off of uncollectible receivables which shall be executed as follows.

a) The total amount to be written-off shall be up to 1% (one percent) of the enterprise's paid-up capital at the beginning of the financial year or up to Birr 100,000,000 (one hundred million Birr), whichever is the lesser.

b) The Board must make a decision within a minimum of one month after reviewing the receivable write-off request, which has been investigated by the investigation committee and supported by the recommendation of the Board's Audit Committee.

c) If the Board approves the write-off request, whether in part or in full, it shall notify the Holding Company within thirty (30) days by submitting a written document specifying the compelling reasons for the write-off, the date of



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

ለሆልዲንግ ኩባንያው በሰላሳ ቀናት ጊዜ ውስጥ በመላክ ማሳወቅ ይኖርበታል።

መ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ዳይሬክተሮች ቦርድ ጠንካራ የብድር ፖሊሲና የተሰብሳቢ ሂሳብ ወቅታዊ የክትትል ስርዓት መኖሩን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

4) የልማት ድርጅቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲሰርዝ ከተሰጠው ስልጣን በላይ የሆኑ እና እስከ ብር 200,000,000 /ሁለት መቶ ሚሊዮን/ የሚደርሱ ተሰብሳቢ ሂሳቦች በሆልዲንግ ኩባንያው ወይም በተቆጣጣሪ መስሪያ ቤት ዋና ሥራ አስፈፃሚ ይሰረዛሉ።

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት የሚቀርበው የስረዛ ጥያቄ በቂ ዝርዝር ማስረጃዎች፣ ማብራሪያዎች እንዲሁም የዳይሬክተሮች ቦርድ አስተያየትና ምክረ-ሀሳብ ተያይዞለት ለሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ለተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ቀርበው ውሳኔ ማግኘት አለባቸው።

6) የሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ ዋና ስራ አስፈጻሚ ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች ዳይሬክተሮች ቦርድ ተጣርቶ ለሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ የቀረበን የተሰብሳቢ ሂሳብ ስረዛ ጥያቄ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የራሱን ኮሚቴ በማቋቋም እንደገና እንዲጣራ ማድረግ ይችላል።

7) ለሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ከተሰጠው ስልጣን ከብር 200,000,000 /ሁለት መቶ ሚሊዮን ብር/ በላይ የሆኑ መሰብሰብ የማይችሉ ተሰብባቢ ሂሣቦች ለሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ ቦርድ ቀርበው የስረዛ ውሣኔ ይሰጥባቸዋል።

approval, and the amount written off, accompanied by other necessary and relevant supporting evidence.

d) The Board of Directors of a state-owned enterprise must ensure the existence of a robust credit policy and a timely monitoring system for accounts receivable.

4) Accounts receivable that exceed the write-off authority granted to the Board of Directors of the enterprise, up to an amount of ETB 200,000,000 (two hundred million), shall be written off by the Chief Executive Officer of the Holding Company or the Supervisory Authority.

5) The request for write-off submitted in accordance with sub-article 4 of this article must be presented to the Chief Executive Officer of the Holding Company or the Supervisory Authority, accompanied by sufficient detailed evidence, explanations, as well as the comments and recommendations of the Board of Directors, in order to obtain a decision.

6) The Chief Executive Officer of the Holding Company or the Supervisory Authority may, when it find it necessary, establish its own committee to re-investigate a receivable write-off request that has been investigated by the Board of Directors of the State-Owned Enterprises and submitted to the Holding Company or the Supervisory Authortity.

7) Uncollectible receivable accounts exceeding the ETB 200,000,000 (two hundred million Birr) decision-making authority granted to the Chief Executive Officer of the Holding Company or the Supervisory Authority shall be submitted to the Board of the Holding Company or the Supervisory Authority for a write-off decision.



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 መሰረት የሚቀርቡ ተሰብሳቢ ሂሳቦች ከበቂ ዝርዝር ማስረጃዎች እና ማብራሪያዎች እንዲሁም ከሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ አስተያየትና የውሣኔ ሃሳብ ጋር ለሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ ቦርድ ቀርበው ውሣኔ ይሰጥባቸዋል።

9) ተሰብሳቢ ሂሳቦች ከመዝገብ በሚሰረዙበት ወቅት ተቀባይነት ያለው የሂሳብ አመዘጋገብ ስርዓትን በመከተል ተገቢው የሂሳብ ምዝገባ ማስተካከያ መደረግ አለበት።

8) Receivable accounts submitted in accordance with sub-article 7 of this article shall be presented to the Board of the Holding Company or the Supervisory Authority, accompanied by sufficient detailed evidence and explanations, as well as the comments and recommendations of the Holding Company or the Supervisory Authority, for a decision.

9) When receivables are written off the books, the proper accounting entry adjustment must be made by following an acceptable accounting recording system.

## 7. <u>በልዩ ሁኔታ ተሰብሳቢን ስለመሰረዝ</u>

1) በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 4 እስከ 7 የተደነገገው ቢኖርም የሆልዲንግ ኩባንያው ወይም የተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ ቦርድ በሚከተሉት ሁኔታዎች የልማት ድርጅቶችን ተሰብሳቢ ለአንድ ጊዜ ብቻ ሊሰርዝ ይችላል፡-

   ሀ) የተሰብሳቢ ሂሳቡ የቆይታ ጊዜ ይህ መመሪያ ፀድቆ ተፈፃሚ እስከሆነበት ቀን ድረስ አስር ዓመት እና ከዚያ በላይ ያለፈው ከሆነ፤ እና

   ለ) ከተሰብሳቢዎቹ ብዛት፣ ውስብስብነት፣ የማስረጃ እጥረት እና ከሚወስዱት ጊዜ እና ገንዘብ አንፃር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 እና 5 የተደነገጉትን ሁኔታዎች ለማሟላት አስቸጋሪ ስለመሆኑ የልማት ድርጅቱ ዳይሬክተሮች ቦርድ ሲታመንበት፤ እና

   ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የተገለጹት ሁኔታዎች መሟላታቸውን የሚያሳይ ዝርዝር ሪፖርት ለልማት ድርጅቱ ዳይሬክተሮች ቦርድ መቅረብ አለበት፤

## 7. <u>Write-off under Special Conditions</u>

1) Notwithstanding the provisions stipulated under Articles 4 to 7 of this Directive, the Board of the Holding Company or the Supervisory Body may, on a one-time basis only, write off the receivables of Enterprises under the following conditions;

   a) If the aging period of the receivables is ten years or more by the effective date of this Directive;

   b) When the Board of the Enterprise is convinced that it is difficult to fulfill the conditions stipulated under Articles 4 and 5 of this Directive due to the volume, complexity, lack of evidence, and the time and cost required for the receivables; and

   c) A detailed report showing the fulfillment of the conditions specified under sub-article 1 (b) of this Article must be submitted to the Board of the Enterprise;

2) When a write-off request is submitted pursuant to this Article, the Board of the



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

2) በዚህ አንቀጽ መሰረት ለስረዛ ጥያቄ ሲቀርብ የልማት ድርጅቱ ዳይሬክተሮች ቦርድ ከጥያቄው ጋር ዝርዝር ማስረጃዎችን በማካተት ለሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ለተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ ቦርድ ማቅረብ አለበት።

3) የሆልዲንግ ኩባንያው ወይም የተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ ቦርድ በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚቀርብለትን ጥያቄ በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል።

4) በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሰረት ለሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ለተቆጣጣሪው ባለስልጣን የሚቀርቡ ማናቸውም የተሰብሳቢ ሂሳቦች ስረዛ ጥያቄዎች፣ ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባለው እና ሊራዘም በማይችል በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ውሳኔ አግኝተው መጠናቀቅ አለባቸው።

## ክፍል ሦስት

## ተከፋይ ሂሳብን ከሂሳብ መዝገብ ስለመሰረዝ

### 8. ተከፋይ ሂሣቦች ስለሚሰረዙበት ምክንያቶች

1) ተከፋይ ሂሳቦች የሚሰረዙት ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ ወይም ከዚያ በላይ በማስረጃ ማረጋገጥ ሲቻል ብቻ ነው ፡ -

ሀ) ዕዳው በፍትሐ-ብሔር ህግ በቁጥር 1845 ስለ ይርጋ በተደነገገው መሠረት እንዲከፈል ጥያቄ ሳይቀርብ ሲቀር፤ ወይም

ለ) ባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ወይም ድርጅቱ ሲፈርስ እና በሕግ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሕጋዊ ወራሽ ወይም የሂሳብ አጣሪ ሳይቀርብ ሲቀር ወይም እንደማይቀርብ ሲረጋገጥ፤ ወይም

ሐ) የመንግሥት የልማት ድርጅቱ ከባለመብቱ ጋር ባደረገው ድርድር አቅራቢው የተከፋይ ሂሳቡን ለመተው ፍቃደኛ ሲሆን፤ ወይም

Enterprise shall submit the request to the Board of the Holding Company or the Supervisory Body by including detailed evidence.

3) The Board of the Holding Company or the Supervisory Body shall examine and render a decision on the request submitted to it pursuant to this Article.

4) Any requests for receivable account write-offs submitted to the holding company or the supervisory authority, in accordance with the provisions of this Article, shall be fully adjudicated and finalized strictly within a non-renewable three-year period from the date of issuance of this Directive

## Chapter Three

## Write-Off of Payables from the Book of Accounts

### 8. Grounds for Write-Off of Payables

1) Payables may be written-off only under one or more of the following grounds, supported by documented evidence:

a) When the payable has not been legally claimed for payment, as stipulated under Article 1845 of the Civil Code regarding the statute of limitations;

b) When the rightful creditor passes away or the organization is dissolved, and a legal heir or liquidator is not presented or is confirmed not to be presented within the time limit set by law;

c) When the creditor agrees to waive the Payable amount following negotiation with the State-Owned Enterprises,



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

መ) ፍርድ ቤት ለዕቃው ወይም የአገልግሎቱ አቅራቢ ክፍያ እንዳይፈጸም ሲወስን፤ ወይም

ሠ) ተከፋይ ሂሳብ በሂሳብ አያያዝ ወይም በጽሕፈት ስህተት፣ በድግግሞሽ ወይም በሰነድ አለመጣጣም ምክንያት የተፈጠረ መሆኑ በመደበኛ ምርመራ ሲረጋገጥ እና ማንኛውም ወገን ጥያቄውን በሕግ ሊያስረዳ ወይም ሊያረጋግጥ ካልቻለ፤ ወይም

ረ) ተከፋይ ሂሳብ ዕቃዎች፣ አገልግሎቶች ወይም ሌላ ተፈጻሚነት ያለው ጥቅማ ጥቅም ላልተገኘበት የገንዘብ መጠን ሲሆን እና የተሟላ የሰነድ ክለሳ ጠያቂው መብት እንደሌለው ሲያረጋግጥ።

2) ተከፋይ ሂሳቦች ሊሰረዙ የሚችሉት ሁሉም አስፈላጊ እርምጃዎች መጠናቀቃቸውን የሚያሳዩ የጽሑፍ ማስረጃዎች ተደግፎ በሚደረግ የተሟላ ምርመራ ሂሳቦቹ ዋጋ የሌላቸው፣ የማይከፈሉ ወይም የሌሉ መሆናቸው ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

## 9. <u>ተከፋይ ሂሳቦችን ከሂሳብ መዝገብ የመሰረዝ ስልጣን</u>

የተከፋይ ሂሳቦች ስረዛ፣ በእያንዳንዱ የክፍያ መዝገብ የገንዘብ መጠን ላይ በመመስረት በሚከተሉት የሥልጣን እርከኖች መሠረት ይጸድቃል፡-

1) በአጣሪ ኮሚቴው ተጣርተው ተከፋይ አለመሆናቸው ወይም ሊከፈሉ አለመቻላቸው በበቂ ማስረጃ የተረጋገጡ ዕዳዎች ከመዝገብ እንዲሰረዙ በድርጅቱ ቦርድ ይወሰናል።
2) የመንግሥት የልማት ድርጅቱ ቦርድ በአጣሪ ኮሚቴው ተጣርቶና በቦርድ ኦዲት ኮሚቴ የውሳኔ ሃሳብ ተደግፎ የቀረበለትን የተከፋይ ሂሳብ በገንዘብ መጠን ሳይገደብ ስረዛ ጥያቄ ቢያንስ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት።
3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተደነገገው ቢኖርም ጥቃቅን የተከፋይ ሂሳብ

d) When a court rules that payment should not be made to the supplier of the goods or services.

e) When the payable is confirmed through formal investigation to have arisen from an accounting or clerical error, duplication, or documentation inconsistency and no party can legally substantiate the claim;

f) When the payable relates to an amount for which goods, services, or other enforceable consideration were never received, and a complete documentary review confirms non-entitlement of the claimant.

2) Accounts payable may be written off only when a comprehensive investigation, supported by written evidence demonstrating that all necessary measures have been completed, confirms that the payables are null and void, unpayable, or non-existent.

## 9. <u>Power for Write-Off of Payables from the Book of Accounts</u>

Write-off of payables shall be approved according to the following levels of authority, based on the monetary value of each payable record:

1) Payables that have been investigated by the investigation committee and confirmed with sufficient evidence to be not payable or uncollectible by the creditor shall be decided by the Enterprise's Board to be written off the books.
2) The Board of the State-Owned Enterprises must make a decision within a minimum of one month on the request for a Payable write-off, without having any threshold limitation, which has been investigated by the



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

በተናጠል የሂሳብ መዝገብ መሰረት የገንዘብ መጠኑ እስከ ብር 10,000 /አስር ሺህ/ በሚሆንበት ጊዜ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሂሳቡ ሊከፈል አለመቻሉን ካመነበት፤ ሂሳቡ የማይከፈል ስለመሆኑ በቂ ጥረት ስለመደረጉ በአጣሪ ኮሚቴ ማጣራት ሳያስፈልገው እና በንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገጉት አስገዳጅ ሁኔታዎች መሟላት ሳይጠበቅባቸው በቀጥታ ከመዝገብ መሰረዝ ይችላል፤ ሆኖም በአንድ የፋይናንስ ዓመት የጠቅላላ የጥቃቅን የተከፋይ ሂሳብ የገንዘብ ድምር መጠን ከብር 500,000 /አምስት መቶ ሺ. ብር/ ሊበልጥ አይችልም።

4) የመንግሥት የልማት ድርጅት የዳይሬክተሮች ቦርድ በዚህ አንቀጽ ድንጋጌ መሰረት ከሂሳብ ላይ እንዲሰረዙ የተጠየቁትን ጥያቄዎች በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ያጸደቀው እንደሆነ የተወሰነበትን ቀን፣ ከሂሳብ ላይ እንዲሰረዝ የተወሰነውን የገንዘብ መጠን፣ የተከፋዩን ስም ዝርዝር እና ከሂሳብ ላይ ለመሰረዝ ግዴታ የሆነበትን ምክንያት በጽሑፍ ሰነድ በማዘጋጀት ከአስፈላጊ እና አግባብነት ካላቸው ማስረጃዎች ጋር ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ በሰላሳ ቀናት ጊዜ ውስጥ በመላክ ማሳወቅ ይኖርበታል።

5) ስረዛው እንደጸደቀ ተገቢ የሆኑ የሂሳብ ማስተካከያዎች ወዲያውኑ መመዝገብ እና ውሳኔው በተላለፈበት የፋይናንስ ዓመት በሚመለከታቸው የፋይናንስ ደረጃዎች መሠረት የፋይናንስ ሪፖርቶች ውስጥ መገለጽ አለባቸው።

6) የዳይሬክተሮች ቦርድ ያልተረጋገጡ ወይም ደጋፊ ማስረጃ የሌላቸው ሊከፈሉ የሚገቡ ሂሳቦች እንዳይከማቹ ለመከላከል ጠንካራ የዕዳ ማረጋገጫ፣ የውል መረጃ አያያዝ እና የክፍያ ማስታረቂያ ሥርዓት መዘርጋቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

investigation committee and supported by the recommendation of the Board's Audit Committee.

3) Notwithstanding what is stated in Sub Article 1 and 2, when the monetary amount of a petty payable, based on a single account record, is up to Birr 10,000 (Ten Thousand Birr), the Chief Executive Officer's Management can directly write off the account without the need for an investigation committee to verify that sufficient effort was made regarding payment or without the need for the fulfillment of the mandatory conditions provided under sub-article 1. However, the total cumulative monetary amount of all petty payables in a single financial year shall not exceed Birr 500,000 (Five Hundred Thousand Birr).

4) If the Board of Directors of the State-Owned Enterprises approves the requests submitted for write-off under this Article, whether partially or fully, it must prepare a written document detailing the date of the decision, the monetary amount decided to be written off, the name of the payee, and the mandatory reason for the write-off, and must notify the Ethiopian Investment Holdings by sending the document along with necessary and relevant evidence within thirty (30) days.

5) Proper accounting adjustments shall be recorded immediately upon approval and disclosed in the financial reports of the financial year in which the decision is made in accordance with the applicable financial standards.

6) The Board of Directors shall have the responsibility to ensure the implementation of a strong liability verification, contract data management, and payable reconciliation



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

system to prevent the accumulation of unverified or unsupported payables.

10. **የመጠየቅ መብት መጠበቅ**

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ወይም 9 መሰረት የሚፈፀም ተከፋይ ሂሳብን ከሂሳብ መዝገብ የመሰረዝ እርምጃ አግባብነት ባለው ሕግ ወይም በውል መሰረት መብቱ በተነካ ወገን ሊቀርብ የሚችል የመጠየቅ መብት አያስቀርም።

10. **The Right to Claim**

The action of writing off a payable account from the accounting records pursuant to Article 8 or 9 of this Directive shall not preclude the right of a party whose rights have been affected from claiming his rights under the applicable law or contract.

## ክፍል አራት
## የንብረት ሂሳቦችን ከሂሳብ መዝገብ ስለመሰረዝ

## Chapter Four
## Write-off of Asset Accounts from the Book of Accounts

11. **ንብረትን ከመዝገብ ለመሰረዝ የሚቀርቡ ምክንያቶች**

1) የመንግስት የልማት ድርጅቶች ክምችት በሚከተሉት ምክንያቶች ከሂሳብ መዝገብ ሊሰርዙ ይችላሉ፡-

ሀ) በቴክኖሎጂ ለውጥ ወይም በሌላ ምክንያት ዕቃዎች ጊዜ ሲያልፍባቸውና ጥቅም ላይ የማይውሉ ወይም አገልግሎት የማይሰጡ እና ለሌላ አካል በሽያጭ ሊተላለፉ የማይችሉ መሆናቸው ሲረጋገጥ፤

ለ) በመጓጓዝ ላይ ያለ ዕቃ ሲጠፋና ይህም በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል ሲረጋገጥ ወይም በአቅራቢው የማይተካ መሆኑ ሲረጋገጥና በኃላፊነት የሚጠየቅ አካል ሳይኖር ሲቀር፤

ሐ) ከንብረት ወይም ክምችት ክፍል ዕቃ ሲጠፋ ወይም ሲጎድል እና ይህም ኃላፊነት በተሰጠው አካል ሲረጋገጥ፣ እና በኃላፊነት የሚጠየቅ አካል ሳይኖር ሲቀር፤ ወይም

መ) ለክምችት ጉድለት ተጠያቂ ነው የተባለ ግለሰብ በፍርድ ቤት ውሣኔ ነፃ ሲሆን፤

ሠ) በሰው ሰራሽ ወይም በተፈጥሮ አደጋ ሲወድም እና ይህም በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል ሲረጋገጥ።

11. **Reasons for Asset Write-Off from the Books**

1) State-Owned Enterprises may write off Inventory/Stock from the book of accounts for the following reasons:

a) When inventory has become obsolete due to technological change or other reasons, and are confirmed to be unusable, non-serviceable, or cannot be transferred to another party through sale;

b) When goods in transit are lost, and this is confirmed by a legal body, or when the supplier confirms that the goods are non-replaceable, and there is no responsible party to be held liable;

c) When goods are lost or deficient from the property inventory section which has been confirmed by the authorized government body, and there is no party to be held liable; or



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

2) የመንግስት የልማት ድርጅት የረጅም ጊዜ ንብረት በሚከተሉት ምክንያቶች ከሂሳብ መዝገብ ሊሰርዝ ይችላል፡-

ሀ) በሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ ውሳኔ የረጅም ጊዜ ንብረቶች ለሦስተኛ ወገን ያለ ክፍያ እንዲተላለፍ ሲደረግ፤

ለ) ንብረቱ የጠፋ፣ የተሰረቀ፣ የወደመ ወይም የፈረሰ ሲሆን እና ማንኛውንም ወገን ተጠያቂ ለማድረግ በማይቻልበት ጊዜ፤

ሐ) በሰው ሰራሽ ወይም በተፈጥሮ አደጋ ሲወድሙ ይህም አግባብ ባለው የመንግስት ተቋም ሲረጋገጥ፤

መ) በመገንባት ላይ ያሉ ንብረቶች ወይም በሂደት ላይ ያሉ ሥራዎች በቋሚነት ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉ፣ ሊመለሱ የማይችሉ ወይም በንግድም ሆነ በሥራ ክንውን ረገድ አዋጭ እንዳልሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሠ) ግዙፋዊ ኃልወት የሌላቸው ንብረቶች፣ ፈቃዶች፣ ሶፍትዌሮች ወይም መብቶች በቋሚነት ጥቅም ላይ መዋል የማይችሉ ወይም በሕግ ረገድ ዋጋ የሌላቸው ሲሆኑ፤

## 12. ንብረቶችን ከመዝገብ የመሠረዝ ሥልጣን

1) የልማት ድርጅት የዳይሬክተሮች ቦርድ ንብረቶችን ከመዝገብ ሊሰርዝ ይችላል።

2) የመንግሥት የልማት ድርጅት የዳይሬክተሮች ቦርድ በዚህ አንቀጽ መሰረት ከሂሳብ ላይ እንዲሰረዙ የቀረበ ጥያቄን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ካፀደቀው የተወሰነበትን ቀን፣ ከሂሳብ ላይ እንዲሰረዝ

d) When an individual alleged to be responsible for the asset deficiency is acquitted by a court decision.

e) When destroyed by the man-made or natural disaster and when this is confirmed by the relevant government organ.

2) State-Owned Enterprises may write off Non-current Asset from the book of accounts for the following reasons:

a) When Non-current Asset are transferred to a third party without payment upon a decision by the Holding Company or the Supervising Authority;

b) When the asset is lost, stolen, destroyed, or damaged and no party can be held liable;

c) When they are destroyed by man-made or natural disasters, and this is confirmed by the appropriate government institution.

d) When assets under construction or work-in-progress are legally confirmed to be permanently unusable, non-recoverable, or no longer commercially or operationally viable;

e) When intangible assets, licenses, software, or rights become permanently unusable or legally invalid

## 12. Authority for Write-Off of Assets from the Books

1) The Board of Directors of the State-Owned Enterprises may write off assets from the books.



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

የተወሰነውን የገንዘብ መጠን፣ የንብረቱን ዝርዝር እና ከሂሳብ ላይ ለመሰረዝ ግዴታ የሆነበትን ምክንያት በጽሑፍ ሰነድ በማዘጋጀት ከአስፈላጊ እና አግባብነት ካላቸው ማስረጃዎች ጋር ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ በሰላሳ ቀናት ጊዜ ውስጥ በመላክ ማሳወቅ ይኖርበታል።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ከመዝገብ የሚሰረዘው የረዥም ጊዜ ንብረት በግመታ ዘዴዎች የሚተመነው የእያንዳንዱ ትክክለኛ የተናጠል ዋጋ 50,000,000 ብር (ከሃምሳ ሚልየን ብር) በላይ በሚሆንበት ጊዜ፤ ንብረቶቹ ከመዝገብ ሊሰርዙ የሚችሉት የልማት ድርጅቶች ዳይሬክተሮች ቦርድ ለሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ ቀርቦ ሲያጸድቅ ብቻ ነው።

4) ክምችት ወይም የረጅም ጊዜ ንብረቶች በዚህ አንቀጽ መሠረት በመጥፋት፣ በመሰረቅ ወይም በቆጠራ ጉድለት ምክንያት ከመዝገብ ቢሰረዙም፤ እነዚህ የተሰረዙ ንብረቶች በሚመለከታቸው ሕጎች እና የአሰራር ሥርዓቶች መሠረት ከስረዛ በኋላ የሚደረግ ክትትል እና ቁጥጥር ይደረግባቸዋል።

5) የንብረቱን ዝርዝር ሁኔታ፣ የስረዛውን ምክንያት፣ የምርመራ ግኝቶችን፣ የተሰረዘውን የገንዘብ መጠን እና የሚጠበቀውን ተፅዕኖ ጨምሮ ስረዛን የሚፈቅዱ ሁሉም ውሳኔዎች በሰነድ ተደግፈው በሠላሳ (30) ቀናት ውስጥ ለሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ለተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤቱ መቅረብ አለባቸው።

**2)** If the Board of Directors of the State-Owned Enterprises approves the requests submitted for write-off under this Article, whether partially or fully, it must prepare a written document detailing the date of the decision, the monetary amount decided to be written off, the asset details, and the mandatory reason for the write-off, and must notify the Ethiopian Investment Holdings by sending the document along with necessary and relevant evidence within thirty (30) days.

**3)** Notwithstanding what is stipulated under sub-article 1 of this article, when the fair value of each of the single non-current asset as determined by the valuations method to be written off from the record is more than 50,000,000 (fifty million Birr); the assets can only be written off from the record after they are approved by the Holding Company or the Supervisory Authority after the submission by the State owned Enterprises Board of Directors.

**4)** Notwithstanding that stocks or fixed assets are written off under this Article on the grounds of loss, theft, or inventory deficiency, such written-off assets shall remain subject to post-write-off monitoring and follow-up in accordance with applicable laws and procedures.

**5)** All decisions authorizing write-off must be documented and submitted to the Holding Company or Supervising Authority within thirty (30) days, including asset details, write-off justification, investigation findings, the amount written-off, and expected impact.



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

## 13. ስለ ንብረት አወጋገድ

የመንግስት የልማት ድርጅት የንብረት አወጋገድ በፌደራል የመንግሥት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ሕግ መሰረት ተፈፃሚ ይደረጋል።

## ክፍል አምስት
## ስለቅድመ-ጥንቃቄዎች እና ስለ ሂሳብ አጣሪ ኮሚቴ

### 14. ከሂሳብ መዝገብ የሚሰረዙ ሂሳቦችን ስለማጣራት

1) የመንግሥት የልማት ድርጅት ኃላፊዎች ሊሰበሰብ የማይችል ሂሣብ እንዳይኖር የማድረግ ተቀዳሚ ኃላፊነት አለባቸው።
2) በዚህ አንቅጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ጥረት ተደርጐ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ውስጥ ሊሰበሰብ የማይችል ሂሣብ ሲፈጠር በወቅቱ ከመዝገብ የመሠረዝ እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ አለበት።
3) ተሰብሳቢ ሂሣቦች፣ ተከፋይ ሂሣቦች እና የንብረት የመዝገብ ዋጋ ከሂሳብ መዝገብ ከመሠረዙ በፊት የሚያጣራና የውሣኔ ሃሣብ የሚያቀርብ የሂሳብ አጣሪ ኮሚቴ መቋቋም አለበት።
4) አጣሪ ኮሚቴው ከሂሳብ መዝገብ የሚሰረዙ ሂሳቦችን አጣርቶ የሚያቀርበው ሪፖርት ስለ ትክክለኛነቱ በማስረጃዎች የተደገፈና በቃለ-ጉባዔ የተረጋገጠ መሆን አለበት።
5) በአጣሪ ኮሚቴው የሚቀርበው ሂሣብ ስረዛ ጥያቄ ለዳይሬክተሮች ቦርድ ከመቅረቡ በፊት የህግ አስተያየት የተሰጠበት መሆኑን እና ሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ ካወጣቸው ፖሊሲዎች አኳያ በተገቢ ደረጃ ተጣርቶ የቀረበ ስለመሆኑ የዳይሬክተሮች

## 13. Disposal of Assets

The disposal of assets of Stateowned Enterprises shall be carried out in accordance with the Federal Government Procurement and Property Administration laws.

## Chapter Five
## Precautionary Measures and the Accounting Investigation Committee

### 14. Investigation of Accounts to be Written Off the Books

1) Officials of the State-Owned Enterprises have the primary responsibility to ensure that uncollectible accounts do not exist.
2) If, despite the effort mentioned in sub-article (1) of this Article, an uncollectible account arises within the State-Owned Enterprises, timely action must be taken to write it off the books.
3) An Accounts Investigation Committee that reviews the Receivables, Payables, and the Carrying Amount of Assets and submits recommendations must be established before they are written off the book of accounts.
4) The report submitted by the Investigation Committee regarding the accounts to be written off the books must be supported by evidence for its accuracy and confirmed by a minute of the meeting.
5) Before the write-off request submitted by the Investigation Committee is presented to the Board of Directors, the Board's Audit Committee must ensure that a legal opinion



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

ቦርድ የኦዲት ኮሚቴው በማረጋገጥ የውሳኔ ሃሳብ አስደግፎ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት።

has been given and that the request has been properly investigated in light of the policies issued by the Holding Company or the Supervising Authority, and shall present it to the Board with its recommendation.

## 15. <u>ሂሣብ አጣሪ ኮሚቴ ስለማቋቋም</u>

1) የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተሰብሳቢ ሂሳቦች፣ ተከፋይ ሂሳቦች እና የንብረት የመዝገብ ዋጋ ከሂሳብ መዝገብ ከመሠረዙ በፊት አጣርተው የሚያቀርቡ ከአምስት ያላነሱ አባላት ያሉበት የሂሳብ አጣሪ ኮሚቴ መቋቋም አለበት።
2) የሂሳብ አጣሪ ኮሚቴው የሚቋቋመው ቦርዱ የሂሳብ ምርመራ እንዲደረግ ሲፈልግ ብቻ ሲሆን፣ የሥራ ዘመኑም ቦርዱ የሰጠው የሂሳብ ምርመራ ሥራ እስኪጠናቀቅ ድረስ ይሆናል።
3) የአጣሪ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለቦርዱ ይሆናል።፤
4) የድርጅቱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሂሳብ ምርመራ እንዲደረግ እንዲሁም የምርመራ ኮሚቴው አባላት ዝርዝር ለቦርዱ የውሳኔ ሐሳብ ማቅረብ ይችላል።
5) የአጣሪ ኮሚቴው አባላት በፋይናንስ፣ በሂሳብ አያያዝ፣ በውስጥ ኦዲት፣ በሕግ ጉዳዮች ወይም ከጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት ባላቸው የሥራ ክንውኖች ላይ በቂ ልምድ እና ብቃት ያላቸው ግለሰቦችን መካተት አለባቸው። እንደ አስፈላጊነቱ ቦርዱ የድምፅ የመስጠት መብት የሌላቸው የውጭ ባለሙያዎችን በጊዜያዊነት ሊመድብ ይችላል።
6) የሂሳብ አጣሪ ኮሚቴው ሥራውን ሲያጠናቅቅ የመጨረሻ ሪፖርቱን እና የውሳኔ ሐሳቡን ለቦርዱ ያቀርባል። ሪፖርቱ የሚከተሉትን በግልጽ ማሳየት አለበት፡-

ሀ) የተመረመሩ ሂሳቦች፤

ለ) ለስረዛ የቀረቡ የገንዘብ መጠኖች፤

## 15. <u>Establishment of Accounts Investigation Committee</u>

1. An Accounts Investigation Committee, consisting of not less than five members, must be established to investigate and report on the Receivables, Payables, and the Carrying Amount of Assets of State-Owned Enterprises before they are written off the book of accounts.rd.
2. The Accounts Investigation Committee shall be established only when the Board requires an account investigation, and its term of office shall be until the completion of the account investigation work assigned by the Board.
3. The Investigation Committee shall be accountable to the Board.
4. The Enterprise's Chief Executive Officer may propose to the Board a decision to investigate an account, as well as the list of members for the Investigation Committee.
5. Members of the Accounts Investigation Committee shall include individuals with adequate experience and competence in finance, accounting, internal audit, legal affairs, or operations relevant to the subject matter. Where necessary, the Board may appoint external experts on a temporary basis without voting rights.
6. Upon completion of its work, the Accounts Investigation Committee shall submit its



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

ሐ) ለስረዛው ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች እና የሕግ መሠረቶች፤

መ) ተጠያቂ የሆኑ ሰዎችን ወይም የቁጥጥር ድክመቶችን መለየት፤ እና

ሠ) የቀረቡ የማስተካከያ እና የመከላከያ እርምጃዎች።

7) የሂሳብ አጣሪ ኮሚቴ አባላት ከጥቅም ግጭት ነፃ መሆን አለባቸው፤ በማንኛውም በሚመረመር ሂሳብ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የግል ጥቅም ያለው ማንኛውም አባል ጥቅሙን መግለጽ ያለበት ሲሆን፣ ያንን ሂሳብ በሚመለከቱ ውይይቶች ወይም ውሳኔዎች ላይ መሳተፍ የለበትም።

final report and recommendations to the Board. The report shall clearly indicate:

a) the accounts examined;
b) the amounts proposed for write-off;
c) the reasons and legal basis for write-off;
d) identification of any responsible persons or control weaknesses; and
e) suggested corrective and preventive measures.

7. Members of the Accounts Investigation Committee shall avoid conflicts of interest; Any member who has direct or indirect personal interest in the account under investigation shall disclose such interest and shall not participate in deliberations or decisions relating to that account.

## 16. <u>የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት</u>

ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1) ሁሉንም ተዛማጅ ውሎችን፣ ደረሰኞችን፣ የደብዳቤ ልውውጦችን፣ የሕግ ሰነዶችን እና የሂሳብ መዝገቦችን መገምገም፤
2) ሁሉም ተመጣጣኝ የሆኑ ሂሳብን የማስመለስ፣ የመፍታት፣ የማስታረቅ እና የማስወገድ አማራጮች ተሞክረው መክሸፋቸውን ማረጋገጥ፤
3) ) የችግሩን መንስኤዎች መለየት፣ ይህም የቁጥጥር ድክመቶችን ወይም ተጠያቂ የሆኑ ግለሰቦችን ማካተት አለበት፤
4) የስረዛ ጥያቄ ከመቅረቡ በፊት መጠባበቂያ ሂሳብ መያዙን መገምገም፤ እና

## 16. <u>Roles and Responsibilities of the Committee</u>

The Committee shall have the following roles and responsibilities:

1) review all relevant contracts, invoices, correspondence, legal documents, and accounting records;
2) verify that all reasonable recovery, settlement, reconciliation, and disposal options have been attempted;
3) identify the causes of the problem, including any control weaknesses or responsible individuals;
4) assess whether a provision has been created before write-off is requested; and



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

5) ለቦርዱ የሚቀርብ የጽሑፍ ሪፖርት እና የውሳኔ ሐሳብ ማዘጋጀት፡፡

## 17. <u>የሂሳብ አጣሪ ኮሚቴ አሰራር ሥርዓት</u>

1) የሂሳብ አጣሪ ኮሚቴው ሥራውን የሚያከናውነው በቦርዱ በሚሰጥ የጽሑፍ የሥራ መመሪያ መሠረት ይሆናል።
2) የቦርዱ ኦዲት ኮሚቴ የሂሳብ አጣሪ የኮሚቴውን ሪፖርት መገምገም እና ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት የጽሑፍ የውሳኔ ሐሳቡን ለቦርዱ ማቅረብ አለበት።
3) የሂሳብ አጣሪ ኮሚቴው ለእያንዳንዱ የተለየ ምርመራ የሚቋቋም ሲሆን፣ የሚያገለግለውም የመጨረሻ ሪፖርቱን እስኪያቀርብ ድረስ ብቻ ይሆናል።
4) የሂሳብ አጣሪ ኮሚቴው በቃለ-ጉባኤ እና በተዛማጅ ማስረጃዎች የተደገፈ በፊርማ የጸደቀ የጽሑፍ ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት።
5) የሂሳብ አጣሪ ኮሚቴ አባላት በማንኛውም ምርመራ ላይ ከመሳተፋቸው በፊት ማንኛውንም የጥቅም ግጭት መግለጽ ያለባቸው ሲሆን፣ አግባብነት ባለው ሁኔታ ራሳቸውን ከምርመራው ማግለል ይኖርባቸዋል።
6) የሂሳብ አጣሪ ኮሚቴው ሥራውን ለማጠናቀቅ አስፈላጊ የሆነ ማንኛውንም መዝገብ፣ ሰነድ ወይም ሠራተኛ በሕግ በተፈቀደው ገደብ ውስጥ የማግኘት መብት ይኖረዋል።
7) የሂሳብ አጣሪ ኮሚቴው ስብሰባውን፣ የመስክ ጉብኝቱን፣ የተገመገመ ማስረጃን ወይም መደምደሚያን በሚመለከት ተገቢ የሆነ መዝገብን መያዝ ያለበት ሲሆን በሥራ ሂደት የተጠቀመባቸውን ሰነዶች በጥንቃቄ መጠበቅ አለበት።

5) prepare a written report and recommendation for submission to the Board.

## 17. <u>Working Procedures of the Accounts Investigation Committee</u>

1) The Accounts Investigation Committee shall conduct its work in accordance with written terms of reference issued by the Board.
2) The Board Audit Committee shall review the Accounts Investigation Committee report and provide its written recommendation to the Board prior to decision-making.
3) The Accounts Investigation Committee shall be constituted for each specific investigation and shall serve only until submission of its final report.
4) The Accounts Investigation Committee shall prepare a written and signed report supported by minutes and relevant evidence.
5) Accounts Investigation Committee members shall declare any conflict of interest before engaging in any investigation and shall recuse themselves where applicable.
6) The Accounts Investigation Committee shall have access to all records, systems and staff necessary to complete its work within legal constraints.
7) The Accounts Investigation Committee shall keep proper records of its meetings, site visits, evidence reviewed, and conclusions, and shall preserve its working papers in a secure manner.



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

# ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 18. ማስተካከያ ስለማድረግ

1) ማንኛውም የዚህ መመሪያ ድንጋጌ ባለመብት የሆነ ሶስተኛ ወገን አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት መብቱን ከመጠየቅ ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ተሰብሳቢ ሂሳቡን ከመሰብሰብ ወይም በባለዕዳው ላይ ሕጋዊ እርምጃ ከመውሰድ አያግድም።
2) በዚህ መመሪያ መሠረት ከመዝገብ የተሰረዘ ተሰብሳቢ ሂሣብ ወይም ተከፋይ ዕዳ ባለዕዳው ሂሳቡን ገቢ ካደረገ ወይም ለባለመብቱ የዕዳ ክፍያ ከተፈጸመ ሂሣቡ በተገቢው የሂሣብ አሠራር ማስተካከያ ይደረግበታል፤

### 19. ሰነዶች አያያዝ፣ መዝገቦችን የመጠበቂያ ጊዜ እና ተጠያቂነት

1) እያንዳንዱ የስረዛ ውሳኔ የምርመራ ኮሚቴው ሪፖርትን፣ የኦዲት ኮሚቴ የውሳኔ ሐሳብን፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔን፣ የሆልዲንግ ኩባንያው ወይም የተቆጣጣሪ መሥሪያ ቤቱ ፈቃድን (እንደ አስፈላጊነቱ) እና የተመዘገቡ የሂሳብ ማስተካከያዎችን ጨምሮ በተሟሉ ሰነዶች መደገፍ አለበት፤
2) ከስረዛ ጋር የተያያዙ ሁሉም መዝገቦች፣ የሥራ ሰነዶች ማስረጃዎች እና ፈቃዶች፣ ስረዛው ከጸደቀበት የፋይናንስ ዓመት መጨረሻ ጀምሮ ቢያንስ ለአስር (10) ዓመታት መቀመጥ አለባቸው።
3) በቸልተኝነት፣ በሥልጣን አላግባብ መጠቀም ወይም በማጭበርበር ድርጊት ምክንያት ያለ በቂ ምክንያት ተሰብሳቢ ሂሳቦች፣ ሊከፈሉ የሚገቡ ሂሳቦች ወይም ንብረቶች እንዲሰረዙ

# Chapter Six

## Miscellaneous Provisions

### 18. On Making Adjustments

1) Nothing in this Directive shall be construed to prevent a third-party creditor from enforcing its rights under applicable laws, nor shall it bar the state-owned enterprise from recovering its receivables or asserting its legal remedies against the debtor.
2) If a Receivable or Payable that has been written off the books according to this Directive is subsequently collected from the debtor or paid to the creditor, an adjustment shall be made to the accounts using the proper accounting procedure.

### 19. Documentation, Record Retention and Accountability

1) Every write-off decision shall be supported by complete documentation, including the Investigation Committee report, Audit Committee recommendation, Board resolution, approval by the Holding Company or Supervising Authority (where applicable), and accounting entries made.
2) All records relating to accounts written-off, including working papers, evidence, and approvals, shall be retained for a minimum period of ten (10) years from the end of the financial year in which the write-off was approved, unless a longer period is required by other laws.
3) Any official or employee who, through negligence, abuse of authority, or fraudulent conduct, causes unjustified write-off of



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

የሚያደርግ ማንኛውም ኃላፊ ወይም ሠራተኛ፣ በሚመለከተው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።

4) ስረዛዎች ተደጋጋሚ የቁጥጥር ግድፈቶችን ወይም ሥርዓታዊ ድክመቶችን የሚያሳዩ በሚሆንበት ጊዜ የመንግስት የልማት ድርጅቱ ዳይሬክተሮች ቦርድ የውስጥ ቁጥጥርን ማጠናከር፣ የአሰራር ሥርዓቶችንመከለስ፣ ስልጠና መስጠት እና እንደ አስፈላጊነቱ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን መውሰድን ጨምሮ የማስተካከያ እርምጃዎች መወሰዳቸውን ማረጋገጥ አለበት።

receivables, payables or assets shall be subject to liability in accordance with applicable laws.

4) Where write-offs reveal repeated control failures or systemic weaknesses, the Board of the Enterprise shall ensure that corrective actions are taken, including strengthening internal controls, revising procedures, providing training and, where appropriate, applying disciplinary measures.

## 20. ሪፖርት ስለማቅረብ

በየፋይናንስ ዓመቱ በዳይሬክተሮች ቦርድ ደረጃ ከመዝገብ እንዲሰረዙ ውሣኔ የተሰጠባቸውን፣ ለሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ ተላልፈው ውሣኔ ያገኙትን ተሰብሳቢ ሂሳቦችን፣ ተከፋይ ሂሳቦችንና፣ የንብረት ሂሳቦችን ዝርዝር የሚገልፅ ሪፖርት ውሣኔ ከተሰጠ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለሆልዲንግ ኩባንያው ወይም ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ መቅረብ አለበት።

## 20. Submission of Reports

A detailed report on Receivables, Payables, and Asset Accounts for which a write-off decision was made at the Board level, and those transferred to and decided upon by the Holding Company or the Supervising Authority in each fiscal year, must be submitted to the Holding Company or the Supervising Authority no later than one month after the decision is made.

## 21. ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም: :

## 21. Repealed Directives

Any directive or customary practice which contradicts this directive shall not be applicable on matters covered under this Directive.



Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026

## 22. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በገንዘብ ሚኒስቴር ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ**
**መስከረም፣ 2019 ዓ.ም**

**አህመድ ሺዴ**
**የገንዘብ ሚኒስቴር**
**ሚኒስትር**

## 22. <u>Effective Date</u>

This Directive shall be effective from the date it is registered with the Ministry of Justice and uploaded on the website of the Ministry of Finance.

**Done at Addis Ababa**

**September; 2026**

**Ahmed Shide**
**Minister,**
**Ministry of Finance**



*Uploaded on the Website of Ministry of Finance on 01 October 2026*